Australian Government
Department of Social Services



# ጾታዊ ጥቃት

## አውስትራሊያ ውስጥ ማንኛውም ሰው ላይ ጾታዊ ጥቃት ማድረስ በህግ የተከለከለ ነው፡፡

የጾታ ጥቃት የሚፈጽም ማንኛውም ወንድም ሆነ ሴት እስር ቤት ሊገባ ይችላል፡፡

| |
|---|
| እርስዎ ወይም አንድ የሚያውቁት ሰው አደጋ ላይ እንደሆነ ካወቁ **000** ብለው ፖሊስ ጋር ይደውሉ፡፡<br>የአውስትራሊያ ፖሊሶች ደህንነትን የሚያስጠብቁና ሊታመኑ የሚችሉ ናቸው፡፡<br>ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ነጻ የምክር አገልግሎትና መረጃ ለማግኘት በ**1800 737 732** ላይ 1800RESPECT ብለው ይደውሉ፡፡<br>አስተርጓሚ በነጻ ማግኘት ከፈለጉ **131 450** ይደውሉ፡፡ |

## የአውስትራሊያ መንግስት (Australian Government) በማንኛውም ሁኔታ ውስጥ ጾታዊ ጥቃትን አይታገስም፡፡

ጾታዊ ጥቃት ካለግለሰቡ ስምምነትና ፈቃድ ውጪ በግለሰቡ ላይ የሚደረግ ጥቃት ነው፡፡ በተጨማሪም በህይወት አጋር፣ በትዳር ጓደኛ ወይም በቤተሰብ አባል ላይ ጾታዊ ጥቃት ማድረስ ህገ-ወጥ ድርጊት ነው፡፡

ጾታዊ ጥቃት የሚከተሉትን ሊጨምር ይችላል፡-

- አንድን ሰው ወሲብ ወይም ጾታዊ ድርጊቶችን እንዲፈጽም ማስገደድ፤
- ማንኛውንም ሰው ጾታዊ ምስሎችን እንዲመለከት ማስገደድ፤ ወይም
- ከህጻን ልጅ ጋር ወሲብ መፈጸም ወይም በጾታዊ ድርጊቶች መካፈል፤

## ሴቶችም ከወንዶች እኩል መብት አላቸው፡፡

ወንዶችም ሆኑ ሴቶች በአውስትራሊያ ህግ እኩል ይታያሉ፡፡

እያንዳንዱ ሰው ከቤተሰቡ አባላት፣ ከጓደኞቹና ከዘመዶቹ ጋር ገንቢና ስጋት የሌለበት ዝምድና የመመስረት መብት አለው፡፡ ጥቃት መፈጸም በምንም ዓይነት እንደ ተራ ነገር አይታይም። የትኛውም ሰው ቢሆን ሲያመናጭቁት ወይም ጉዳት ሲደርስበት ተቀብሎ መኖር የለበትም፡፡

## አውስትራሊያ ውስጥ፣ ባህል ላይ ያተኮሩ በዚህ ረገድ እርዳታ ሊሰጡ የሚችሉ አገልግሎቶች አሉ፡፡

**1800RESPECT** የአውስትራሊያ ብሄራዊ ጾታዊ ጥቃት፣ የቤተሰብ እና የቤት ውስጥ ጥቃት የምክር አገልግሎት (Australia's national sexual assault, family and domestic violence counselling service) ሰጪ ነው፡፡ ምስጢራዊነቱ የተጠበቀ ነፃ የስልክ እና የኦንላይን የምክር አገልግሎት እና መረጃ ይሰጣል፡፡ ምክር ሰጪዎቹ ያዳምጡዎታል፤ ጥያቄዎችዎን ይመልሳሉ እንዲሁም በአካባቢዎ ወደሚገኙ ሌሎች እገዛ ሰጪዎች ይመሩዎታል፡፡

በ**1800 737 732** ይደውሉ ወይም የ፡-በ **www.1800RESPECT.org.au**.አድራሻ **1800RESPECT ድረ-ገጽን** ይጎብኙ።

## አስተርጓሚ ያስፈልግዎታል?

የትርጉም እና የማስተርጎም አገልግሎት (**Translating and Interpreting Service**) (TIS)ን በስልክ ቁጥር **131 450** ደውለው ያነጋግሩ፡፡ የ TIS ባልደረባ የሆነ አንድ አስተርጓሚ ከሌሎች አገልግሎቶች ጋር እንዲነጋገሩ ሊረዳዎት ይችላል፤ ይሁንና፡ TIS የምክር አገልግሎት አይሰጥም፡፡ ሁሉም የስልክ ጥሪዎች ከክፍያ ነፃ ከመሆናቸውም በላይ ጉዳያችሁ በሚስጥር ይያዛል።